# ከንቲባ ገብሩና አፍሮ አሜሪካውያን

« ኢትዮጵያ ሕዝብዋ በየጊዜው በሚነሣው ጦርነት፣ በንዳድና በበሽታ የሚያልቀው ብዙ በመሆኑ ከሕዝብ እጥረት የተነሣ ብዙ ባዶ መሬት አለን። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በእርሻና በከብት እርባታ ስለሆነ እርሻውንና ከብት እርባታውን በዘመናዊ ሁኔታ ለማከናወን የሠለጠነ የሰው ኃይል ያስፈልገናል። በብዛት የሚፈሱት ወንዞች ሁሉ ተገድበው በረሃው እንዲለማ፣ ወበው እንዲጠፉ፣ ሕዝቡንም የሥራ ሙያ የሚያስተምርና የሚያሠለጥን የሰው ኃይልና ገንዘብ ያስፈልገናል። ከልማቱ ጋር የመንገድ ሥራ ይከተላል። ይህንን ከሥራ ላይ ለማዋል ጊዜ ይጠይቃል። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ጃፖንና እንደ ቻይና እንደ ህንድም ያሉት ሀገሮች የሕዝብ ብዛት አስጨንቋቸዋል። የኢትዮጵያ አቅዋም የዓለም ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) አባል እንደመሆናችን መጠን የተወሰነ ሕዝብ እንድናሠፍር ብንጠየቅ እምቢ ማለት አንችልም። ካስፈቃዳችን ከምንገደድ በፈቀዳችን ገንዘብና የሥራ ዕውቀት ያላቸውን ጥቁር አሜሪካኖች እየመረጥን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ በር ብንከፍትላቸው ኢትዮጵያውያን በጭር ጊዜ ሥራም ሆነ ዕውቀት ያገኛሉ። ልማቱም ይፋጠናል። ወጣቱም ወደ ከተማ እየመጣ የሰው ሎሌ ከሚሆን በገጠር የራሱ ጌታ ሊሆን ይጣጣራል»

ይህን ሃሳብ ለኢትዮጵያ መንግሥት በጽሁፍ ያቀረቡት ከንቲባ ገብሩ ደስታ ነበሩ። ዘመኑም 1912(1) ነው። ከንቲባ አሜሪካንን በጎበኙበት ጊዜ ባዩትና በታዘቡትም ጥቃት እጅግ ተነክተዋል። ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ የአገራቸው ኋላ ቀርነት የሚያቆስላቸውን ያህል የጥቁሮቹ ወንድሞቻቸውም ሁናቴ እጅግ ከነከናቸው። ለኢትዮጵያም ለጥቁር አሜሪካኖችም ልባቸው እኩል ተሰቀለ።

*ከንቲባ፡ ገብሩ፥ የኢትዮጵያ፡ ቅርስ።*

---

*ከ.ዳዊት፡ ገብሩ ።*

*አዲስ፡ አበባ፥ 1985 ዓ. ም. ገጽ፡ 165*

(1) 1916 ብለው፡ ያንብቡ።

፩ - *ትርጉም፤*

ከመስመር፡ አንድ፥ እስከ፡ መስመር፡ ስምንት፡ ያለውን፡ ጽሑፍ፡ ወደ፡ ፈረንሳይኛ፡ ይተርጉሙ።

፪ - *ጥያቄ፤*

ለሚቀጥሉት፡ ጥያቄዎች፡ ባማርኛ፡ መልስ፡ ይስጡ።

አ - የደብዳቤው፡ ደራሲ፥ ባ፩ኛ፡ መደብ፡ በብዙ፡ ቍጥር፡ «እኛ» እያሉ፡ ጽፈዋል። ለምን፡ ይኾን ?

በ - የዛሬይቱ፡ ኢትዮጵያ፥ በደራሲው፡ ጊዜ፡ ከነበረችው፡ ኢትዮጵያ፡ በምን፡ ትለያለች ?

ገ - ከንቲባ፡ ገብሩ፥ ላገራቸው፡ ሕዝብና፡ ለጥቍር፡ አሜሪካውያን፡ እኩል፡ መቈርቈራቸው፡ ለምን፡ ይመስልዎታል ?